# ከህግ ወሳኔ በፊት የተካሄደ ጣልቃ ገብነት

ቶሎሳ ኡርጌሳ

**Utolosa@yahoo.com**

ለህሊና እስረኞች እሚገታለሁ ባይ ነው — /Freedom Now/ "ፍሪደም ናው" የተሰኘው አክራሪ ኒዩ ሊበራል ተቋም፡፡ ዋና መቀመጫውን ዋሽንግተን ዲሲ ያደረገው ይህ ተቋም፤ ሰሞኑን አንድ ክስ አሊያም አቤቱታ መሳይ ነገር አቅርቧል፡፡ ተከሳሿ ደግሞ የፅንፈኛ ኒዩ-ሊበራል ኃይሎች "የዕለት እንጀራ" ወደ መሆን የተሸጋገረችው የፈረደባት ሀገራችን ናት፡፡

ተቋሙ ከመሰንበቻው በመንድስታቱ ድርጅት ያለ አግባብ የታሰሩ ሰዎችን ጉዳይ ለሚያጠናው ግብረ ኃይል ስለ አቶ እስክንድር ነጋ ጉዳይ አቤት ብሏል፡፡ የአሜሪካ ድምጽ እንደዘገበው የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ማሪያም ተርነርም "የጋዜጠኛውን" ጉዳይ ለመከታተል ኢትዮጵያ መግባታቸውንም ገልጸዋል፡፡

የድርጅት ገራገር ምግባር አንድ የሀገሬን ተረት አስታወሰኝ፡፡ ነገርን ነገር ያነሳው የለ። አዎ! 'አልሰሜን ገባ በለው' ይላል የሀገሬ ሰው— ፀሃይ የሞቀውን፣ ሀገር ያወቀውንና ተብላልቶ ያለቀለትን ጉዳይ እንደ አዲስ ይዞ ብቅ የሚል አርፋጅ እንግዳን፡፡

አዎ! በእኔ እምነት 'ፍሪደም ናው' አርፋጅ እንግዳ አሊያም አላዋቂ መርዶ ነጋሪ ነው፡፡ እንዲያ ባይሆንማ ለወራት የተወያይንበትን፣ በቅርበት ስንከታተለው የቆየውን፣ የእነ እስክንድር ነጋን ጉዳይ ይዞ የማታ ማታ ብቅ ባላለ ነበር፡፡ እናንተዬ ማን ነበር ጀማሪ ሯጭን ጃን ሜዳ ውሰደው ያለው?— መቼም ሌላኛው የልብ ወዳጁ "ሂዩማን ራይትስ ዎች" ሊሆን አይችልም።

ያም ሆነ ይህ አርፋጁ የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ነኝ ባዩ 'ፍሪደም ናው' በጠበቃነት እንደቆመ የተመጻደቀው ለአቶ እስክንድር ነጋ ብቻ አይደለም፡፡ ስለ በርካቶች ጠዋት ማታ የሚጸልይና የሚለምን መስሎ የቀረበው አዲሱ ድርጅት፤ በዓለም ውስጥ የህሊና እስረኛ አድርጎ ከመዘገባቸው መካከል ስለ ሃያዎቹ ብቻ ሸንጡን ገትሮ እየሞገተ መሆኑን ገልጿል፡፡ እስክንድር ነጋ ታዲያ ከሃያዎቹ መካከል አንዱ መሆኑ ነው፡፡

እርግጥ ለሰው ልጆች ደህንነት፣ ፍትህ፣ ሠላምና ሰብዓዊ መብት መሚገት መልካም ነገር ነው፡፡ እንዲያውም ከመልካም ነገሮች ሁሉ የላቀው መልካም ነገር ነው፡፡ ይህን መቃረን ጤነኝነት አይደለም፡፡ ክፋቱ ግን በክብሩ የሰው ልጆች መብት ስም ለመነገድ የራስን ድብቅ አጀንዳ ለመሸቀጥ መጣደፍ፣ መሯሯጡ ላይ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ስለ እስክንድር ነጋ ጠበቃ ለመቆም የተነሳው 'ፍሪደም ናው' ብቻ አይደለም፡፡ ዜናውን አርፋዶ የሰማ ይመስላል- "ኤሌክትሮኒክስ ፍሪደም ፋውንደሸን' የተባለ ዓለም አቀፋዊ ድርጅትም አብሮት ተሰልፏል፡፡

የዓለም አቀፍ የፕሬስ ነጻነት አቀንቃኝ መሆኑን የሚያትተው ድርጅቱ፣ የኢትዮጵያ መንግስት እስክንድር ነጋን በነጻ ያሰናብትልን ዘንድ ወዳጆቹ ሁሉ ከነኑ ተሰልፈው አቤት እንዲያባብሉት አሊያም እንዲያማልዱት ጥሪ አቅርቧል፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ ተቋሙ "ወዳጆቼ" ያላቸው እነማን እንደሆኑ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ልብ እንደሚልልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። እናም እንዲህ ዓይነቱን "ተባብረን የኢትዩጵያን የህግ የበላይነትን እንደፍጥጥ" ጥሪን ወቸው ጉድ እንጂ ከቶ ምን ማለት እንችላለን? …

ተቋሙ በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ አማላጅነቱ እንደማይሰራ ቆሌው ነግሮት ነው መሰል የአሜሪካ መንግስት ኢትዮጵያን የማግባባት ስራ ሰርቶ ጋዜጠኞችን እንዲያስፈታለት ግልጽ ደብዳቤ መጻፉንም አልሸሸገም፡፡ ሃያላን ሀገራት በሰው ሀገር ህጋዊ አሰራር ውስጥ ጣልቃ ገብተው አንዲፈተፍቱ ተማፅኗል ማለት ነው፡፡ እስቲ አሁን ማን ይሙት በወንጀል ተጠርጥሮ በህግ ከለላ ስር ያለውን ለማስፈታት አማላጆችን አሊያም ሃያላን ሀገራትን ማማተር ሞኝነት እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይችላል፡፡

በእርግጥ 'ኤሌክሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽን' ገራገር ተቋም አደለም፡፡ ደፋር እንጂ፡፡ ምክንያቱም የፍትህ ስርዓቱንና ሀገራችን የሚንቅ ዕብሪተኛ ድርጅት ባይሆን ኖሮ ህግ ነጻ ብሎ ያላሰናበተውን ግለሰብ ከውሳኔ በፊት የራሱን ብይን በመስጠት 'የፕሬስ ነጻነት ብሔራዊ ዓርማ' ብሎ ባደባባይ ባልዘመረ ነበር፡፡

ግና ተቋሙ በምን መስፈርት፣ የትና ከእነማን ጋር አወዳድሮ ብሔራዊ ጀግናችንን ድንገት በዚህ ወቅት እንዳገኘልን ባይነግረንም፤ አቶ እስክንድርን ለነጻነት ሟችና የጋዜጠኝነት ተምሳሌት አድርጎ አምካሾቶታል፡፡

ውድድሩ ምናልባትም በሰማይ ቤት አሊያም በአክራሪዎቹ ዓለም ተካሂዶ እንደሆነ መረጃ የለኝም፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን በሀገረ ኢትዮጵያ እስክንድር ነጋ የተጨበጨበለት ጋዜጠኛ መሆኑን እውቅና የሰጠ ውድድር አልተካሄደም — ሁከትና ብጥብጥን በመቀመር ብቃቱ ተጠርጥሮ በህግ ጥላ ስር መዋሉ እንጂ።

ድርጅቱ ያሻውን መሾም መብቱ ነው፡፡ እስክንድር ነጋን ለምን ወደደው አይባልም፡፡ የጥፋት አጋሩ፣ በወንጭፍ ባህር ማዶ ሆኖ መልዕክት እየላከ የሚያስፈጽምበት የሩቅ ወዳጁ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ጠንቅቆ የሚያውቀው ህግና ህግ ብቻ እንጂ እኔ ስላልሆንኩኝ የማላውቀው ጉዳይ ውስጥ ገብቼ መፈትፈት አልሻም፡፡

ግን በአንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ። እስክንድር ነጋን ያከናውናቸው በነበራቸው ስራዎቹ አውቀዋለሁ፡፡ ቢያንስ ጋዜጠኛ አደለም፡፡ በእርግጥ የጋዜጠኝነት ሙያን አጥንቷል፡፡ ጋዜጠኝነትን ያጠና ሁሉ ግን ጋዜጠኛ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡

ጋዜጠኛ እውነትን የሚጽፍ ስለ ሃቅ የሚኖር መሆኑን ትልቁ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነኝ ባዩ ‘ኤሌክትሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽን’ ይቅርና እኔም መደዳው ዜጋ እረዳለሁ፡፡ ግና ተጠርጣሪው አቶ እስክንድር በብዕረኝነትና በአመጸኝነት ስም የበተናቸውን የጥፋት መልዕክቶችን አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም ብዙ ጊዜ በልዩ ልዩ የህትመት ውጤቶች አንብቢያለሁ- ታዝቤያለሁም፡፡

አይኑን በጨው ታጥቦ በፀረ - ሠላምና በሽብር ምግባራቸው ተጠርጥረው በፍትህ ጥላ ስር ያሉ ግለሰቦችን ለማወደስ የተጣደፈው ተቋሙ ግን ሌሎች ኢትዮጵያውንን ለመሳደብም አላቅማማም፡፡ በርካታ ጋዜጠኞች ሀገራቸውን ለቀው ሲሰደዱ ወይም ዝምታን ሲመርጡ እሱ ግን የብዕር ጀግንነቱን እንደገፋበት አስረድቷል፡፡

ሁሉም ጋዜጠኞች በበሬ ወለደ ተረት-ተረት ሀገራችንን ለማተራመስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አዝኖባቸዋል፡፡ አፍሮባቸዋል፡፡ ግና የትኛው ጋዜጠኛ ወደ የትኛው ሀገር በኪሳራ ምክንያት እንደተሰደደ ሊነግረን አልደፈረም፤ዝምታን የመረጡት እነማን እንደሆኑም አልገለጸልንም— የውንጀላ ዓላማው መሰረቱ ሃቅ ሳይሆን የርዕዮተ-ዓለም ጉዳይ ነውና።

ግና እንዲህ ዓይነቱ አሉባልታ በእኔ እምነት ተራ የመንደር ወሬ ይመስለኛል—ጉዳዩ በሃሳብ ዓለም ካልሆነ በስተቀር የማይጨበጥና የማይዳሰስ አልባሌ ውንጀላ ነውና። ያም ሆነ ይህ እስቲ እጅግ በጣም ካስደመሙኝ የተቋሙ “ገራገርነቶች” ቀጣዩን ላስከትል። ‘ኤሌክትሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽንን’ የእስክንድር ነጋን ሁኔታ በአካል ተገኝቶ ለማረጋገጥ አልቻለም። ራሱ በዘገባው እንዳመነው ጠይቆ ፈቃድ ባለማግኘቱ ይሁን ስራ በዝቶበት መግለጽ ባይችልም፤ ጀግናዬ ያለውን በወንጀል ተጠርጣሪ “ጋዜጠኛ” በቅርበት ለመጎብኘት አልቻለም፡፡

ግን በነሲብ እርግጠኛ ነው፡፡ በዚህም እስክንድር ነጋ ደህንነቱ እንዳሰጋው ገልጿል። እናንተዬ ጉድ’ኮ ነው- መረጃ ባይኖረውም፤ “ጋዜጠኛውን” ማዬት ባይችልም ማረሚያ ቤቶቻችንን አያምንም፡፡ በእርሱ እምነት ጥቁሮች ስለሆንን ብቻ ጨካኞች ነን፡፡ ሰብዓዊነት እንደማይሰማንም አድርጎ ቆጥሯል፡፡

እናም በህልሙ ይሁን አሊያም የዲሲው ውቃቢ አምላኩ በምን ብልሃት ስለ “ጋዜጠኛው” አካላዊ ሁኔታ እንዳስረዳው ባላውቅም በመልካም ሁኔታ እንደማይገኝ ግን በድፍረት ተናግሯል፡፡ ማለፊያ ርህራሄና መልካም ነብይነት ነው - የማይታየውን ማየት በነብይነት መልክ መገለጥ እንጂ ከቶ ሌላ ምን ይባላል?...

እዚህ ላይ የ‘ኤሌክትሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽንን’ ጉዳይ ለጊዜው ገታ ላድርግና የበሬ ወለደ የጥፋት ማበርተኛውን ‘ፍሪደም ናው’ን አስገራሚ ዲስኩር ላንሳ፡፡ ተቋሙ “ጋዜጠኛውን” ፍጹም እንደማያውቀው ያትታል፡፡ ግና ጋዜጠኛው የጻፈውን ብቻ ሳይሆን በአዓዕምሮው የሚያስበውንም ጭምር (የሆዱን) ጠንቅቆ እንደሚያውቅ መስክሯል- በአደባባይ። እስክንድር ነጋ የጋዜጠኝነት ስራን ብቻ ሲያከናውን የነበረ ብፁዕ ፍጡር እንጂ ጥፋተኝነት እንደማይነካካው ሁሉም ሰው እንዲገነዘብለት በማስታወስ፡፡

እኔ ግን አንድ አልገለጥልህ ያለኝ ነገር አለ፡፡ ነጮችን ረቂቁን የሰው ልጅ ተፈጥሮ ፈልቅቀው ማወቅ የሚችሉት ምግረ ሰናዩን ከምግባረ እብዩ አብጠርጥረው የሚመዝኑበት መስፈሪያቸው ምንድን ነው?— ውይ ታድለው! አጥፊውን ከመልካሙ፣ ክፉውን ከደጉ አይተው ብቻ ይለያሉ - ልክ ጥቁርና ነጭ ብሎ የመረጅ ያህል መሆኑ ነው፡፡ ወዳጄ ሆይ !ምነው እኔም ነጭ በሆንኩ ያስብላል አይደል?... ቂ.ቂ.ቂ....

ነገሩ "ስንተዋወቅ አንተናነቅ" እንደሚባለው ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ በመሰረቱ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት እስክንድር ነጋ ጋዜጠኛ ወይም ብሎገር አይደለም፡፡ ተቋሙ በጋዜጠኝነት ስም ለመነገድ የሚቋምጥ ታዳጊ የኒዮ-ሊበራሊዝም አቀንቃኝ በመሆኑ፤ የጠራ መረጃ ለማሰበሰብ ጊዜ በማጣቱ ወይም ባለመፈለጉ እንጂ ግለሰቡ በክብሩ የጋዜጠኝነት ሙያ የራሱን ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ በማራመድ ሀገርን ለመናድና ዜጎችን ከዜጎች ለማበላት ቆርጦ የተነሳ መሆኑን በተረዳ ነበር፡፡

እርግጡን እንነጋገር ከተባለ እውነቱን መጨዋወት ይኖርብናል፡፡ እናም እደግመዋለሁ፡፡ እስክንድር ነጋ ጋዜጠኛም 'ብሎገርም' አደለም፡፡ በልዩ ልዩ የህትመት ውጤቶች አማካኝነት የራሱን ፀረ - ኢትዮጵያና ፀረ - ሠላም አቋም የሚያንጸባርቅ ግለሰብ እንጂ ጋዜጠኝነትን ማጥናት ጋዜጠኛ ካስባለ ወረቀት እንዳለው አውቃለሁ፡፡ ምግባሩን ግን በወንጀል እንዲጠረጠር ነው ያደረገው— እንደ ተቋሙ ተጣድፌ ፍርድ ለመስጠት ባልችልም፡፡ ትክክል ባይሆንም በብዕሩ የሰበከው ጥፋትን ነው፡፡ ምግባር ከቃል ይቀድማልና ምግባሩ የሚመሰክረው ቀናዒ ኢትዮጵያዊነቱን አይደለም፡፡

አዎ! ለፍትህ ቆሚያለሁ ባዩ 'ፍሪደም ናው' በየትኛው የፍትህ አካል፤ የት በዋለው ችሎት እንደ ዳኘው ባይገልጽም፤ የእስክንድር ነጋን ብፁዕነት በአደባባይ መመስከሩ ድፍረት ይመስለኛል፡፡ የአንድን ሀገር ህዝብና የፍትህ ስርዓት መናቅ ነው፡፡ የህግ ባለሙያ አደለሁምና ስለ ህግ አካሄድ ባላውቅም ህግ የያዘውን ተጠርጣሪ ነጻ አድርጎ መፈረጅ ወንጀልም ይመስለኛል፡፡

ግለሰቡ ወንጀለኛ መሆኑን እየተናገርኩ አይደለም፡፡እንደዚያ የማለት መብቱም ሆነ ሞራሉም የለኝም፡፡ ወንጀለኛ አሊያም ነጻ ብሎ ብይን የመስጠት መብት የሀገሪቱ የፍትህ ስርዓት መሆኑን እገነዘባለሁ። እግረ መንገዴን ግን ለአቶ እስክንድር በህጋዊ ስርዓቱ መሰረት መልካሙን ሁሉ እንዲገጥመው እመኛለሁ፡፡

ለጊዜው የዳኝነቱን ስራ ተወት ላድርገው— ህግና ስርዓቱን ተከትሎ ብይን መስጠት የሚችለው የሚመለከተው አካል ነውና፡፡ ይሁንና ሁላችንም በመገናኛ ብዙሃን እንደተከታተልነው እስክንድር ነጋ በህግ ቁጥጥር ስር የዋለው ህግና ደንብ በሚያዘው መሰረት እንጂ ሃሳቡን በነፃነት ስለገለፀ አይደለም። ከሳሽ ደግሞ ህግ ነው፡፡

የሀገሪቱ የፍትህ ስርዓት ህግና ስርዓትን የማስጠበቅ ግዴታም መብትም አለበትና ግለሰቡን ለክስ መቅረቡ እንደ ጥፋት መቆጠር ያለበት አይመስለኝም፡፡ እናም ዐቃቤ ህግ አለኝ ከሚለው መረጃ ጋር አያይዞ ፍትህ እንዲዳኝለት አቀረበ፡፡ ጉዳዩን ተመልክቶ ግለሰቡን ነጻ አሊያም ወንጀለኛ የማለቱ ኃላፊነት የዳኝነት ስርዓቱ ነው፡፡ በመሆኑም ህግ በያዘው ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የራስን ዳኝነት መስጠት ግን በፍጹም ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ጉዳዩ የህግ ጉዳይ እንጂ የመንግስት ባለመሆኑ፤ መንግስትን በአማላጅ ማስለመንም ያልተለመደ አሰራር ይመስለኛል፡፡

በነገራችን ላይ መንግስት ለማግባባት አማላጅ የላከው 'ኤሌክትሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽን' ብቻ አደለም፡፡ እጅ መንሻ መላኩን ባይናገርም 'ፍሪደም ናው' የተባለውና በተመድ የታሰሩ ሰዎችን ጉዳይ ለሚያጠናው ግብረ ኃይል አቤት ማለቱን የገለጸው ተቋምም አማላጅ መላኩን አልሸሸገም - "ጋዜጠኛውን" ለማስለቀቅ፡፡

ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን በምልጃ ማስፈታት የሚቻል ከሆነ በተቋማቱ ፍላጎት ጣልቃ መግባት አልችልም፡፡ ይሁንና የተቋማቱ ህቡዕ ዓላማ "ጋዜጠኛውን" ለማስፈታት አሊያም አለ የሚለውን የፕሬስ ነጻነት ጥሰትን ለመታደግ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ስለ ሰብዓዊ  መብትና ለፕሬስ ነጻነት እንደሚባትሉ ጠዋት ማታ ቢሰብኩንም ሃቁ ግን "ዶሮን ሲያታልሏት..." መሆኑ ይገባናል፡፡

ጉዳዩ በክቡሩ የጋዜጠኝነትና የሰብዓዊ መብት ስም ተጠልለው ያረጀ የፈጀ የኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካል ኢኮኖሚ ስርዓታቸውን አሜን ብለን ባለመቀበላችን ብቻ የተጠነሰሰ  ሳይሆን፤ የራሳችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር ተከትለን በመጓዝ የተሻለች ሀገርና ኢኮኖሚ መገንባት በመቻላችንና የእነሱን አስተሳሰብ ውድቅ ያደረገ አዲስ መዋቅር በመፍጠራችን ደስተኞች ባለመሆናቸው የሚነሳ መሆኑ ነው፡፡

እናም አንጡራ ሀብታችንን ለመዝረፍ የሚያስችላቸውን የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ለመዘርጋት የሚያስችል አውድና ስርዓት እንዲስፋፋ ጠንክረው ይሰራሉ፡፡ አስተሳሰባቸውን የማይከተል እነሱ የፈበረኩለትን ጫማ ለማጥለቅ (ቢሰፋውም ቢጠበውም) ፈቃደኛ  ያልሆነ መንግስትና ህዝብ በተፈጠረ ጊዜ ታዲያ በፕሬስ ነጻነትና በሰብዓዊ መብት  ጥሰት ተጠልለው በበሬ ወለደ ክሳቸው አፍሪካዊ መንግስታትን ለማጠልሸት ቆርጠው ይነሳሉ፡፡ አንዳንድ የእርዳታ ድርጅቶችና ምግባረ ሰናይ ተቋማትም  ለልማት ስራዎች የሚሰጧቸውን የገንዘብ ድጋፍ ለርዕዮተ-ዓለም ሰበካቸው እንዲያውሉት ያደርጋሉ፡፡

ይህ አካሄዳቸው በበርካታ የአፍሪካና የሩቅ ምስራቅ ሀገራት ከ 1980 ዎቹ ጀምሮ የተስተዋለ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ነው፡፡ ታሪክ እንደሚነግረን ጥቂት የማይበሉ ሀገራት በኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካል- ኢኮኖሚ ስርዓት ለቀውስና ለብጥብጥ ተዳርገዋል፡፡ በስርዓቱ ሃብታቸው ተመዝብሮ የበይ ተመልካች ሆነዋል።

በአንፃሩ ደግሞ ቻይና እና ህንድን የመሳሰሉ የራሳቸውን መንገድ የተከተሉ ሀገሮች ግን ሁላችንም እንደምናየው ከፍተኛ ምጣኔ ሃብታዊ እምርታን እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ሀገራቸውንና ህዝባቸውን የሚመጥን የራሳቸውን ትክክለኛ አቅጣጫ በመከተላቸው በፈጣን የኢኮኖሚ እሽክርክሪት ውስጥ ገብተው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

ሀገራችንና ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት በአሁኑ ወቅት በፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለአክራሪ ኒዩ ሊበራል ሃይሎች ትልቅ የራስ ምታት ነው። ምክንያቱም በእነርሱ እሳቤ ማንኛውም ሀገር ከኒዩ ሊበራሊዝም ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ርዕዮተ-ዓለም ውጪ ማደግ ስለሌለበት ነው።

ግና ይህን የርዕዮተ-ዓለም ልዩነት በሃይል ለመደፍጠጥ በሙብት ጥበቃ ስም መንግስታችንን በማጠልሸት የራሳቸውን አጀንዳ ለማራመድ እንቅልፍ ያጣሉ። የፕሬስ ነፃነት፣ ሰብዓዊ ሙብት፣ የእኛ ዓይነት ዴሞክራሲ...ወዘተ አጀንዳችን ከያሉበት እየነተቱ ያወጣሉ።...እናም እንዲህ ዓይነት ተቋማት ጊዜ ቢያጥራቸው የሚደንቅ አይደለም— ጉዳዩ የመኖርና ያለመኖር ነውና፡፡ የሆድ ጉዳይ ሆድ ይቆርጥ የለ፡፡ አዎ! እንዲያ ማለት ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ በሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ረብጣ እያሸከመ ወደ አፍሪካና መላው የላቲን አሜሪካ ሀገሮች የሚልካቸው የኒዮ-ሊበራሊዝም አቀንቃኝ አለቃ አሊያም የፖለቲካል- ኢኮኖሚ አባት እንዳላቸው መዘንጋት የለብንም፡፡ እናም አጀንዳቸውን እንደ ኮሶ እየመረረንም ቢሆን ለመጋት ፈቃደኛ የማሆን መንግስትና ህዝቦች እንደማያገኙ በተረዱ ጊዜ፤ የከንቱ ክስና የስም ማጥፋት ዘመቻቸውን እንደሚገፉበት ግልጽ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ የ ‘ፍሪደም ነው’ እና የ ‘ኤሌክትሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽን’ ተራ አሉባልታና አቶ እስክንድር ነጋን ለማስፈታት ጠዋት ማታ መባዘን ያው የተለመደው አሰልቺ ውትወታቸው ነው፡፡ በመሰረቱ በኢትዮጵያና በሌሎች መሰል ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ በእኛ እናውቅላችኋለን ሰበብ ሊፈተፍቱ የሚስተዋሉት እነዚህ ተቋማት ብቻ አይደሉም፡፡ ለአብነት ያህል የሰብዓዊ ሙብት ተሟጋች ነኝ ባዩ ‘ሂውማን ራይትስ ዎች’ እና ‘ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ’ ማውሳቱ ተገቢ ነው፡፡

ታዲያ እነዚህ ሁለት ተቋማት በቅርቡ የዓለም ባንክና የአፍሪካ ልማት ባንክ ለሀገራችን የሰጠውን የብድርና የድጋፍ ገንዘብ በይፋ ተቃውመው ነበር፡፡ የማታ ማታም ቢሆን ለጋሽ ድርጅቶቹ እውነታውን በመገንዘባቸውና ለሰብዓዊ ሙብት ቆመናል የማለት ድርጅቶች ጩኸት መሰረተ- ቢስ መሆኑን በማመኑ ጀሮ ዳባ ልበሱ ማለቱ በጄ እንጂ፡፡

አንድ ነገር ግን በግልጽ መገንዘብ የሚገባን ይመስለኛል፡፡ የባህር ማዶ ሰዎችና ተቋማት በወንጭፍ በሚወረውሩት ሀገርን የመበታተን ዘመቻ የሚፈታ ትውልድና ሀገር የለንም፡፡ ሃቁን መላው የኢትዮጵያ ህዝብና የኢትዮጵያ ወዳጆች ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ እናውቀዋለን፡፡ በተራ አሉባልታና በስማ በለው የምንወናበድ ሞኞችም አደለንም፡፡ ለዚህ ሀገር የሚበጀውንና የሚጠቅመንን የምናውቀው እኛ ኢትዮጵያዊንና ኢትዮጵያዊያን ብቻ ነን፡፡

በመጨረሻም አንድ ነገር ማለት እወዳለሁ፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን በየጊዜው በስማ በለው በሚበተኑ የጥፋት መልዕክቶች ሳንደናገጥ ስለ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ግንባታ ስርዓታችን ስር እንዲሰድና የታላቁ መሪያችንን ራዕይ ዕውን እንዲሆን መትጋት ይኖርብናል፡፡

‘ምግባር ከቃል ይቀድማልና’ ማመንና መከተል የሚገባን በተጨባጭ የምናየውን እንጂ፤ ባህር ማዶ ተቀምጠው ሻምፓኝ እየተራጩ በሉዓላዊነታችን ላይ የሚቀልዱትን ‘ፍሪደም ናው’ እና ኤሌክትሮኒክ ፍሪደም ፋውንዴሽን’ን መሆን አይገባም፡፡ ለእኛ ስለ እኛ የሚጨነቅና የሚያስብልን የለም—“ከባለቤቱ በላይ የሚያውቅ ቡዳ” ነው እንዲል የሀገራችን ሰው።